# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር 1/2011

ሰኔ / 2011ዓ/ም

ባህር ዳር

**ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011**

**1. አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 62/1/ሀ እና አንቀጽ 93/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**2. አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ" **ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011** "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3. ትርጓሜ**

በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ወይም በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

1) **"ደመወዝ"** ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም፡፡
2) **" የትራንስፖርት አበል"** ማለት በቀጣሪውና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ ውል ውስጥ በግልጽ የተመለከተ እና ተቀጣሪው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ሥራ ቦታ እንዲሁም ከስራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመጓጓዝ እንዲሁም ተቀጣሪው ሥራውን ለማከናወን መደበኛ ስራ ቦታው በሚገኝበት ከተማ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዘዋወር የሚያስፈልገው የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን በቀጣሪው የሚከፈል አበል ነው፡፡
3) **"የውሎ አበል"** ማለት አንድ ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ ወይም የህዝብ ተመራጭ የተቀጠረበትን ወይም የተመደበበትን ሥራ ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ በሚሄድበት ጊዜ ለምኝታ፣ለምግብ፣ለመጠጥና ለተዛማጅ ወጪዎች የሚከፈል አበል ነው፡፡
4) **"በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ሁኔታው ለጨረር ፣ለበሽታ፣ለ ኬሚካል ልቀት ወይም ብክለት፣ለንጹህ አየር እጥረት ፣ለከፍተኛ ሙቀት ፣ለከፍተኛ ቅዝቃዜ